# የባሕር-በር ጥያቄ ከኢትዮጵያ አንድነት፣ የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ከፀጥታ፣ ከልማትና እድገት ዋስትናነት አኳያ፤

*የግል አስተያየት:- ኢያል ሰው ደሴ　　　　ሰኔ ሁለት-ሽህ-ሦስት ዓ/ም - ክፍል ሁለት*

ስለ-ሆነም የቀይ ባሕር ጠረፎችን ከላይ እስከ-ታችና በምሥራቅም በኩል ከጅቡቲ እስከ ዘይላና ከዚያም ባለፈ ያሉ ወደቦችን ሙሉ-በሙሉ በእነሱ ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ማዋልና ኢትዮጵያን እፍን-እፍንፍን አድርጎ አስጨንቆ መያዝ ነበረባቸው:: አንዴ ያንን ማድረግ ከቻሉና ኢትዮጵያን ማነቆ ውስጥ ካስገቡ በኋላ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ወደ-ውስጥ እየገፉ የውስጥ ትርምስ መፍጠሩ ቀላል እንደሆነ ተገንዝበዋል:: ስሊታቸውም በመጠኑ ሰርቷል:: በመጠኑ ያልኩበት ምክንያት ያ ሁሉ መረባረብ ተደርጎባቸውም እንኳ፣ ቱባ እነሱነታቸውንና አገር-በቀል ዓይነታ እሴቶቻቸውን መበረዝ፣ በመኻላቸው ክፍፍልን መፍጠርና የመሣሰሉ ከባድ ከባድ ጉዳቶችን እንዳደረሱ ቢታወቅም፣ ኢትዮጵያውያንን ሙሉ-በሙሉ ማንበርከክና ኢትዮጵያዊ መንፈስንና ማንነትን ጨርሶ ማክሰም ስላልቻሉ ነው::

በሕወሓት መሪዎች ተንበርካኪና የአገርን ጥቅም ጨርሶ ስሊት ውስጥ ያላስገባና ያላቋጠረ እርምጃ ኤርትራ እንድትገነጠል በማድረግ የአገሪቱን ዜጎች በአንድ ጊዜ እንዲለያዩ ሲያደርጉ፣ የአፋርን ኩሩና አገር-ወዳድ ሕዝብ ያለ አንዳች ጥያቄ ከሁለት ሲከፍሉና ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር ባለቤትነት ሲነቅሉ አንድም የሚያስከትለውን መዘዝ አልተገነዘቡትም አለበለዚያም የሸዓብያን ዓላማ በውክልና አስፈጻሚ ሆነዋል ማለት ነው::

ይኸንን ያበደ እርምጃ በዝምታ ማየትና በኩራት *"እንኳን እኛ ግመሎቻችን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ያውቃሉ"* የተባለለት ወገናቸው የአፋር ብሔረሰብ ከሁለት ተከፍሎ አንደኛው ተገድዶ አዲስ ዜግነት እንዲይዝ መደረጉ ያልተዋጠላቸውና የአፋርን ሕዝብ የአንድነት ጥያቄ ለመደገፍ፣ ኢትዮጵያም በቀይ ባሕር ጠረፍና በሮች ላይ ሊኖራት የሚገባውን የባለቤትነት አንጡራ መብቷን ልታጣ አይገባም በሚል እሳቤ ተነሣስተው አገር-ወዳድ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን የዛሬ አሥራ-አንድ ዓመት ***"የቀይ ባሕር መብት አስጠባቂ ኮሚቴ** - Committee For The Preservation of Ethiopia's Red Sea Coast"* በሚል መጠሪያ የተደራጀና በክቡር አቶ በላይ ዓባይ ሊቀ-መንበርነት የሚመራ (እኔም አባል የሆንኩበት) አካል ተቋቁሞ ለጉዳዩ የሚገባው ትኩረት እንዲሰጠው የተቻለውን ያኸል ማድረጉ ይታወቃል:: ያ ኮሚቴ የተመሠረተውና በተደራጀ መልክ የተንቀሣቀሰው ለጉዳዩ ሥራዬ-ብሎ ልዩ ትኩረት በመስጠት ይሁን እንጂ፣ ኢትዮጵያውያን በአገር-አቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶቻቸው አማካይነትም ይሁን በተናጠል ጥያቄውን በቁጭት ከማንሣት ተቆጥበው እንደማያውቁ ግልጥ ነው::

በእርግጥ የባሕር በር ጥያቄ ሲነሣ እዚኽ ላይ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ለቀይ ባሕሩ የባሕር ጠረፍ ይሁን እንጂ ጉዳዩ ጠበብ ብሎ የወደብ ብቻ ተደርጎ ከታየ በምሥራቁ የአገሪቱ ክፍልም ቢሆን፣ በተለይ ላለፉት ወደ-ሃያ ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ እራሱን ችሎ የሚኖረው የሰሜኑ ሶማሌ ክፍል ሥር እንደ በርበራ የመሰሉ ወደቦችን መጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎች እንደ-ነበሩና አሁንም እንዳሉ ግልጥ ነው:: እንደ-አንዳንድ መረጃዎች ከሆነ ደግሞ ይኸ የሰሜኑ የሶማሌ ክፍል ከኢትዮጵያ ጋር ቢያንስ በኮንፌደሬሽን ለመተሣሰር የጠበቀ ፍላጎት እንዳለና ጥያቄም ለአቶ መለስ ዜናዊ ቀርቦ እንደ-ነበር፣ ሆኖም የተሰጠው ምላሽ እንኳን ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚልን እነሱን (ጥያቄ አቅራቢዎችን) ባስገረመ መልኩ አሉታዊ እንደ-ሆነ ይነገራል::

ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያውያን መራር ትግል የጣልያን ወራሪዎች ከአገራችን ከተባረሩ በኋላ ተነጥላና አዲስ ስም ተሰጥቷት በባዕዳን አገዛዝ ሥር ትገኝ የነበረችው ኤርትራ በኤርትራውያንና በኢትዮጵያውያን የጋራ ትግል ተመልሣ በኢትዮጵያ አገራዊ ክልል ሥር ስትሆን አገሪቱ በጉልበት ተነጥቃ በኖረችው የቀይ ባሕር ጠረፍ ላይ የባለቤትነት መብቷን ማረጋገጥ መቻሏ ግልጥ ነው:: ያም ሆኖ ግን በወቅቱ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች በምሥራቁ የአገሪቱ ክፍል ያለው ክፍተት እንዲደፈን ከማሰብ

አልቦዘኑም፡፡ በመሆኑም በፈረንሣይ ቅኝ ግዛት ሥር የነበረችው ትንሿ ጅቡቲ በሕዝበ-ውሳኔ የወደፊት ዕድሏን ወደ-መወሰን ስትቃረብ የኢትዮጵያ አካል መሆን ስለምትችልበት መንገድና ሁኔታ ከማሰላሰል አልተቆጠቡም፡፡ እንደሚታወቀው ተሥፋፊው የሰኢድ ባሬ መንግሥትም ጉዳዩን በዓይነ-ቁራኛ የሚከታተለውና የበኩሉን ዝግጅት እንደሚያደርግም የሚጠበቅ ነበር፡፡

ጓደኛየ ሽበሽ ኃይሌ እና እኔ ወደ ፈረንሣይ ጦር ትምሕርት ቤት የተላክንበት ምክንያት ከዚኹ ለአገሪቱ ከታሰበ የወደፊት እቅድ ጋር የተዛመደ እንደ-ሆነም በወቅቱ የቀዳማዊ ኃይለ-ሥላሴ አካዳሚ አዛዥ በነበሩት ጄኔራል ግዛው በላይነህ እና የትምሕርትና ዘመቻ መኮንን በነበሩት ጀግናው ሻለቃ (በኋላ ጄኔራል) ደምሴ ቡልቶ አማካይነት በተደረገልን ስንብት ላይ ከተገለጡልን ጥብቅ ማሣሰቢያዎች መኻል ይኸ ዋናው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለዚኹ ጉዳይ ከነበሩ መሰናዶዎች ውስጥ አንዱ ስድስት ሻለቃ የሚሆን ልዩ ጦር እንዲዘጋጅ የነበረው እቅድ ሲሆን ያም በኋላ ደርግ 'ነበልባል' በሚል መጠሪያ አሰልጥኖ ያሰማራው ክፍል እንደ-ነበር ይነገራል፡፡

ያ ሁሉ የሚያሣየው ቅድመ-ሕወሓት/ኢሕአዴግ የነበሩ መንግሥታት አገራቸው ኢትዮጵያ በባለቤትነት የምትቆጣጠረው የባሕር በር እንደሚያስፈልጋት ማመን ብቻ ሣይሆን እንዲኖራትም፣ እስከ-ተቻለ ድረስም ከአላት ላይ ተጨማሪ ለማስገኘት ከማለምና አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ ጥረት ከማድረግ እንዳልቦዘኑ ነው፡፡ ያ ደግሞ ከምንም በላይ አገራቸው በባሕር ጠረፎች ላይ የባለቤትነት ይዞታ ከማጣት ጎውናዋና እድገቷ ላይ የሚያስከትለውን ችግር ከራሷ የሩቅና የቅርብ ታሪክ በተገቢ ከመገንዘብ የመጣ እንጂ ከተስፋፊነት ስሜት የመነጨ አልነበረም፡፡

የጉዳዩን አሣሳቢነት የተሻለ ለማሣየት ያኽል ግልጥ ከሆነው ኤኮኖሚያዊ ዘርፍ ውጭ በአጭሩም ቢሆን በራሷ ቀጥተኛ የባለቤትነት ቁጥጥር ሥር የሆነ የባሕር በር በማጣት ምክንያት ኢትዮጵያ የደረሱባትን የቅርብ ጊዜ ኩኔቶች ማስታወሱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

አንደኛ፡- ጉዳዩ አገራዊ አንድነትን፣ የሕዝብን ሰላም፣ ክብርን፣ ሉዓላዊነትንና ጎልውናን ተፈታታኝ ከመሆኑ አኳያ ሊታይ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ጠረፎች ላይ ያላትን የባለቤትነት ቀጥተኛ ቁጥጥር ባታጣ ኖሮ ኦቶማን ቱርኮችና ከግብፅ ጀምሮ ያሉ የአካባቢ አረቦች ባሕር ተሻግረው የኢትዮጵያን ግዛቶች ለመቆጣጠርና በቀጥታም ይሁን በእጅ-አዙር የውስጥ ሰላማችንን ማደፍረስና ሕዝባችን መከፋፈል ባልቻሉ ነበር፡፡ የወቅቱ የአገሪቱ መሪዎችም ያለ-የሌለ አቅማቸውን እነዚያን በየጊዜው የተቃጡና ያላባሩ ወረራዎች በመከላከል ላይ በመጠመድ ገበሬው እርሻውን፣ ነጋዴውም ንግዱን በመተው ላልተቋረጠ ዘመቻ፣ መፈናቀልና እንግልት በመዳረጉ ሕዝብ እንዲደኸይ፣ የምጣኔ ሃብት እድገትና ማኅበራዊ ኑሮ መሻሻል እንዳይኖር አድርጓል፡፡ አገሪቱ እየቀረቀዘች በመሄዷም ማዕከላዊነት እየተዳከመ ሄደ፡፡ እንደ-ማንኛውም በጦርነት የተጠመደና የውስጥ ሰላሙን ያጣ ሕዝብ ሁሉ ኢትዮጵያውያንም ለቀጣይ ሰላም እጦትና ለድህነት አዙሪት ተዳረጉ፡፡

ማዕከሉ እየተዳከመ ሲሄድ ደግሞ አንድ ሆኖ የቆየው ሕዝብ በተለያዩ መሣፍንትና የጠረፉ ሕዝብም በአብዛኛው ባሕር ተሻግረው በመጡ ባዕዳን ሱልጣኖች አገዛዝ ሥር ተከፋፍለው እንዲገዙ፣ ኢትዮጵያውያን ተለያይተው እንዲኖሩ እና ያም ለቀጣይ ውጥረትና ሐይማኖትን መሠረት ላደረገ ጭምር የእርስ-በርስ ግጭቶችና ጦርነቶች እንዲዳረግ፣ በዚያም ምክንያት ኢትዮጵያውያን በየአካባቢያቸው እንዲታቀቡና በተናጠል ቆመው አዳዲስ የማንነት መታወቂያ እንዲያዳብሩና ኩታ-ገጠም ወገናቸውን እንደ ባዕድ እስከ-ማየት ደረጃ እንዲደርሱ፣ አጠቃላይ ሥልጣኔም እንዲቆምና አገራዊ አንድነት እንዲዳከም ሆኗል፡፡

በዚኸ ምክንያት በሕዝቡ መኻል የነበረው ትሥሥር እንዲላላ በመደረጉ፣ አገራዊ አንድነት በመጥፋቱና ማዕከሉ በመዳከሙም እንግሊዞች ባሕር ተሻግረውና መቅደላ ድረስ ዘልቀው ኢትዮጵያን ለማዋረድ፣ የአገሪቱን ንጉሠ-ነገሥት አፄ ቴዎድሮስን ለመውጋት፣ አልጋ-ወራሹን ልዑል ዓለማየሁን ማርኮ ለመውሰድና ታሪካዊ ቅርሶቻችንንም ለመዝረፍና መሸከም የቻሉትን ያኽል ለመውሰድ በቅተዋል፡፡ በዚያ የውስጥ መዳከምና ማዕከል መርገብ ምክንያትም ከመቶ-አምሣ ዓመታት በፊት ጣልያኖች ባሕር-ምድርን (ምድረ-ባሕር/ሪን -

ኤርትራን) በጉልበት ለመያዝና የቀረችዋ ኢትዮጵያ ላይ ለመዝመት የተሻለ ሁኔታን ሊፈጥርላቸው ችሏል።

ሁለተኛ፡- ለባዕዳን ቀጣይና የማይቆም ወረራ መጋልጥን እንደሚጋብዝና እንደሚያ-ስከትልም ሊጤን ይገባል። በዚኽ ረገድ የዛሬ ሰባ-አምስት ዓመት ጣልያን ኢትዮጵያን በግፍ ስትወር የደረሰውን ማስታወሱ መልካም ይሆናል። ጣሊያኖች አድዋ ላይ የደረሰባቸውን አዋራጅ ሽንፈት ለመበቀል ከአርባ ዓመታት ሙሉ ዝግጅት በኋላ ከኤርትራ ተንደርድረው በኢትዮጵያ ላይ የሰው ዘር ማጥፋት ደረጃ የደረሰ የግፍ ወረራ ሊፈጽሙ የቻሉት ኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባሕር ጠረፏ በአጠቃላይና የባሕር በሮቿ ቀደም-ሲል በሌሎች ባዕዳን፣ በኋላም በእነሱ ሥር በመውደቃቸው ነው። የባሕር ጠረፎቻችንን በመያዝ ኤርትራን ገንጥለው መቆጣጠር በመቻላቸው ያልረኩት ጣልያኖች ኤርትራን በመንደርደሪያነት መጠቀም ብቻ ሣይሆን የራሣችንን ወገኖች ኤርትራውያንን ጭምር አዝማች አድርጎ በመጠቀም ኢትዮጵያ ላይ ግፍ መፈጸም ችለዋል። እነሱም ሆኑ ሌሎች አውሮጳውያንና አረቦች ኢትዮጵያን መቆጣጠር ቢችሉ ኖሮ ኢትዮጵያን በመንደርደሪያነት ተጠቅመው ይዞታቸውን በቀረው አፍሪቃ ለማስፋት ከመጣር እንደማይመለሱ የታወቀ ነው። ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፎቿ ላይ ያላትን የባለቤትነት መብት በመነጠቋና በሮቿ በመዘጋታቸው ምክንያት እሣት ውስጥ እንደተጣለ ላስቲክ ወደ-ውስጥ እየተሸበሸበችና እየተዳከመች መሄዷ ግልጥ ነው።

ሦስተኛ ፡- የባሕር በር እጦት መሠረታዊ ሰብዓዊ ክብርን ለፈተና ከመጣሉ፣ ኀልውናን እግት ከማስያዙ፣ ሉዓላዊነትን አሣልፎ ከመስጠቱና ጥገኛ ከማድረጉ አኳያ የሚኖረው አሉታዊ ሚና ሊታወቅ ይገባል። ሕዝብ ለኀልውናውና ለክብሩ ከባዕዳን ግፈኛ ወራሪዎች ጋር ለሚያደርገው ፍልሚያ በእርዳታ የሚያገኘውን ቀርቶ በራሱ አቅም የሚገዛውን መሣሪያ በፈለገው ጊዜ ማግኘት እንደማይችል ኢትዮጵያውያን በተግባር ያረጋገጡትና በማይሽር ቁጭት የሚያስታውሱት ሃቅ ነው።

የጣሊያን ፋሽስት ወራሪዎች አገራችንን ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ በዕብሪት ሲዘምቱና በሰላማዊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተከለከለ መርዝ ጭስ ሣይቀር በመጠቀም ግፍ ሲፈጽሙ ወረራውና ግፉ እንዲቆም ኢትዮጵያ አባል ለሆነችበት የመንግሥታቱ ማኅበር አቤቱታ ብታቀርብም፣ በዘረኛ አስተሣሰብ የተበከሉ የአውሮጳ መንግሥታት ዘመናዊ መሣሪያ አምራች የሆነችውን ጣልያንና ተራ የቃታ የነፍስ-ወከፍ ጠመንጃዎችን ሣይቀር ከውጭ አገር አምራቾች ከመግዛት ሌላ አማራጭ ያልነበራት ኢትዮጵያ ላይ በሁለቱም ተፋላሚዎች - በግፈኛ ወራሪዋ ጣልያንና የጥቃት ሰለባ በሆነችው ሰላማዊቷ ኢትዮጵያ - ላይ የመሣሪያ እቀባ አድጊያለሁ የሚል ግልጥ የሆነ አድልያኣዊና ዘረኛ ብይን ማስተላለፉ ይታወቃል። በኤኮኖሚ ደካማ የሆነችው ኢትዮጵያ ቆራጥ ሕዝቧ ከጣሊያን ተስፋፊዎች የግፍ ወረራ እራሱን ለመከላከል የሚያስችል መሣሪያ ከመግዛት ሌላ ምርጫ አልነበራትም። ሆኖም ኢትዮጵያ በአላት የደሃ አቅም ከግፈኛ ወራሪዎች እራሷን ለመከላከል የገዛቻቸው የጦር መሣሪያዎች ወደ-ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ትንሿ ጅቡቲ በሯን በመዝጋቷና በመከልከሏ ምክንያት ኢትዮጵያውያን እራሣቸውን ከግፈኛ ወራሪዎች እንዳይከላከሉ ያደረገና ለባዕዳን ውርደት አሣልፎ የሰጠ እኩይ ተግባር በመሆኑ ምን-ጊዜም ሊረሣ የሚገባው ጉዳይ አይደለም።

ባዕዳን ባሕር ተሻግረው ይኽን ሁሉ መዓት በሕዝባችን ላይ ማድረስ የቻሉት፣ ሕዝባችንም እየባሰ ለሚሄድ ድህነት አዙሪት የተዳረገው፣ የአገራችን ጥንታዊ አንፀባራቂ ሥልጣኔ የተገታው፣ የአገሪቷ ዜጎች አንድነታቸውን አጥተው ተከፋፍለው እንዲያድጉ የሆነው፣ የአገሪቱም ኀልውናና ደኅንነት በውጭ ኃይሎች ቀጥተኛና የእጅ-አዙር ጫና ሥር እንዲወድቅ የሆነው፣ ትንሿ ጅቡቲም ወገናቸው የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከባዕዳን ወረራ እራሱን እንዳይከላከል የከፈለበትን መሣሪያ ሣይቀር መከልከል የቻለችውና ሰብዓዊ ክብራችንና ኀልውናችን ላይ ሊወስኑ የበቁት፣ አገራችንም እየኮሰመነች የሄደችው በዋናነት ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፎቿን፣ በተለይም የቀይ ባሕር ወደቦቿን በባለቤትነት በቀጥታ መቆጣጠር ባለመቻሏ ነው።

ይኽ ሁሉ የሚያሣየው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች እንደሚያስቡት በቀውጢ ጊዜ ጅቡቲንም ሆነ፣ በርበራን፣ ሞምባሣን ሆነ ፖርት-ሱዳንን በማንኛውም ጊዜ እና እንደ-ልብ መጠቀም እንደማይቻል ነው። በእርግጥ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችና አንዳንድ

*ደጋፊዎቻቸው እንደሚሉት ከወደብ ባለቤቶች ተዋውለንና ገንዘብ ከፍለን "መጠቀም" ይቻላል። ሆኖም እነኝኸ ወገኖች መገንዘብ ያቃታቸውና ደግመው ደጋግመው ሊረዱት የሚገባው ጉዳይ ዋናዎቹ የወደቦቹ ባለቤቶች ብቻ ሣይሆኑ በተለይ የዓለም ኃያላንና የቅርብና የሩቅ ታዳጊ አገሮች አካባቢያችንን በልዩ ልዩ ምክንያቶች - የተፈጥሮ ሃብት (በተለይም እንደ ነዳጅ ለመሣሰሉ የኃይል ምንጮች) ቅርምት በሚደረግ የተጋጋለ ፉክክርም ሆነ "አክራሪዎችን ለመቆጣጠር" ትኩረታቸውን በሳበበት በአሁኑ ጊዜ ማንኛውም የወደብ ተቆጣጣሪን ባለቤት አገር እንደ ኢትዮጵያ ዓይነቱ "ባዕድ" እንዳይጠቀምበት ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ጫናና እገዳ ማድረግ መቻላቸውን ነው።*

*በተጨማሪም እዚያው ላይ ሊታይ የሚገባው ወደብን ለመጠቀም ውል የሚደረገው በጊዜው ሥልጣን ከያዘ መንግሥት ጋር ነው የሚሆነው። እንደሚታወቀው ደግሞ በአሁኑ ጊዜ "አሉ፣ ልንጠቀምባቸው እንችላለን" የሚባሉት ወደቦች ሁሉ የሚገኙት ዴሞክራሲያዊ ባኅሪ በሌላቸውና ይኸንን ያኸል የሕዝባቸውን ይሁንታ ባላገኙ መንግሥቶች ይዞታ ሥር ነው። ያም ማለት በማንኛውም ጊዜ የመገልበጥ ጨርሶም ከቁጥጥር ውጭ ያሉ ሁኔታዎች ሊከሰቱ የመቻላቸውና "ግልጋሎቱ" በማንኛውም ሰበብ አስባብ ወይም ምንም ምክንያት መስጠት ሣያስፈልግ በአንድ ጊዜ ሊገታ እንደሚችል፣ በተጨማሪም እነዚኸ መንግሥቶች አንዳንዶቹ በሙስና የነቀዙ ሌሎቹም እራሣቸውም እንኳ የተባሉትን ወደቦች ሙሉ-በሙሉ ላይቆጣጠሩበት የሚችል ሁኔታ ሊከሰት የመቻሉ ብቻ ሣይሆን ኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎትን ለመጠቀም የሚከፈል አቅሙ እንኳን ቢኖራት ኢትዮጵያ መክፈል ከምትችለው እጥፍ-ድርብ ለመክፈልና እንዳትጠቀምበት ለማድረግ አቅሙም ፍላጎቱም የሞላቸው ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች እንዳሉም መገንዘብ ያስፈልጋል።*

*ስለ-ሆነም አሁን "አሉ፣ ልንጠቀምባቸው እንችላለን" ብለው የሕወሓት/ ኢሕአዴግ መሪዎች የሚመኩባቸው ወደቦች በዋና ባለቤቶቹ ብቻ ሣይሆን በሌሎች ሦስተኛ ኃይሎችም ጭምር ኢትዮጵያ ልትገለገልባቸው እንዳትችል እንደሚያደርጉ ግልጥ ሊሆን ይገባል። በሁሉም ረገድ እራሷን ያልቻለችው ኢትዮጵያ በባለቤትነት የምትቆጣጠረው የባሕር በር ከሌላት በአገር ውስጥ የማይመረቱ እቃዎችን ለማስገባት ይሁን እነዚኸኑ ለመግዛት እንዲቻል ለውጭ ምንዛሬ የሚሸጡ ጥሬ ሃብቶችና የምርት ውጤቶችን እንደ-አስፈላጊነቱና እንደ-ልብ ለማስተላለፍ አትችልም። ያም ማለት ቀደም-ሲል ጅቡቲ ከወሰደችው የግፍ እርምጃ በተግባር እንደተረጋገጠው የአገርን አንድነትና ፀጥታ ለማስከበር የሚስፈልጉም ይሁን የሕዝብን ጤናና ደኅንነት ለመጠበቅ በጣም አስፈላጊና ነፍስ-አድን የሆኑ መድኀኒቶችና ተመሣሣይ ቁሣቁሶችና ንጥረ-ነገሮችን በተፈለጉበት ጊዜና ፍጥነት ማቅረብ አይቻልም ማለት ነው።*

*ይኸ ዓይነት እክል ደግሞ እንደ-ተራ በወደብ መገልገል አለ-መቻልና የሸቀጥ ልውውጥ መደናቀፍ ዝቅ ተደርጎ የሚታይ ሣይሆን ሠፋ ሲል የባሕር ጠረፎችን፣ አነስ ሲል ደግሞ ወደብን <u>በቀጥታ ባለቤትነት</u> መብት መቆጣጠር አለመቻል የአንድን አገር አንድነት፣ ደኅንነት፣ ሰላምና ብልፅግና አልፎም የሕዝብን ሉዓላዊነት፣ ለባዕዳን አሣልፎ መስጠት ወይም እነዚኸን ቁልፍ እሴቶች በሌሎች በጎ-ፈቃድ ላይ ጥገኛ የሚያደርግና በወለድ-አገድ ያስያዘ፣ ለእግት ያዘጋጀ አደገኛ ስሌት የሚሆነው። ስለዚኸም ነው "የሰው ወርቅ አያደምቅ" እንዲሉ ምን ጊዜም ቢሆን አሁን የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች አሉ የሚሏቸው መገልገያ ወደቦች እንኳን በቀውጢ ጊዜ "በበጎና በሰላም ጊዜ" አዘቦታዊ አገልግሎቶች ማግኘት ሣይቀር በዋና ባለቤቶቹና በነዚኸ ባለቤቶች ላይ ቁጥጥር ባላቸው ሦስተኛ ኃይሎች በጎ-ፈቃድ ላይ ብቻ የተንጠለጠለ መሆኑን ሊረዱት ይገባል የምለው።*

*ኢትዮጵያ በባለቤትነትና በራሷ ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ያለ የባሕር ጠረፍ ቢያንስ የባሕር ወደብ/ወደቦች እስከሌላት/ሏት ድረስ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ሰላም፣ ደኅንነት፣ ፀጥታና የኤኮኖሚ እድገትና ልማት ሊኖራት አትችልም። ያ ሣይሆን የሚደረግ "የልማት" ጥረት ሁሉ ድንጋይ አንገት ላይ በሸምቀቆ አሥሮ ለመዋኘት ወይም በባዶ እግር በእሾህ ላይ ለመሮጥ የመሞከርን ያኸል ወይም በወንፊት ውሃ ለመቅዳት እንደ-መሞከር ከንቱ ድካምና ቀቢፀ-ተስፋ ይሆናል።*

***በክፍል ሦስት ይቀጥላል....***